# በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

## የጎብኚዎች የክፍያ ተመን ሥርዓት
## መመሪያ ቁጥር 490/2013

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
Records Section
የሪከርድና ማህደር ክፍል

መጋቢት 2012 ዓ.ም

# መመሪያ ቁጥር 490/2013

## በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

## የጎብኚዎች የክፍያ ተመን ሥርዓት መመሪያ

ባልተጠና እና ባልተቀናጀ መንገድ የሚወሰኑ የጎብኚዎች የክፍያ ትመናዎች በቱሪዝም አገልግሎት አሠጣጥ ላይ ክፍተት በመፍጠር የሀገሪቱ ገፅታ ላይ ጉልህ ተፅዕኖ ያስከተለ በመሆኑ፤

ተገቢው የጎብኚዎች የክፍያ ተመን ሥርዓት ባለመዘርጋቱ ሀገሪቱ ከቱሪዝም ዘርፍ ማግኘት የሚገባትን ምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ ጥቅሞች እንድታጣ በማድረጉ፤

ወጥነት በሌለው አሰራር የሚወሰኑ የጎብኚዎች የክፍያ ተመኖች በጎብኚዎች ፍሰት፣ የቆይታ ጊዜ እና የእርካታ ደረጃ ላይ አሉታዊ ተፀዕኖዎች እያስከተለ በመሆኑ፤

የጎብኚዎች የክፍያ ተመን አወጣጥ ወጥ፣ ግልፅና ፍትሐዊ በሆነ የአሰራር ስረዓት በመምራት የአገር ውስጥና የዓለም ዓቀፍ ቱሪዝምን ለማስፋፋት አመቺ ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀፅ 30 ንዑስ ቁጥር 9 መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ መመሪያ "የጎብኚዎች የክፍያ ተመን ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 490/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ትርጓሜ</u>

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

   1) "ጎብኚ" ማለት ቱሪስት ወይም ማንኛውም እለታዊ ጎብኚ ነው፡፡

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
Records Section
ሪከርድና ማህደር ክፍል

2) "ቱሪስት" ማለት በቋሚነት ከሚኖርበት አካባቢ ለጉብኝት፣ ለመዝናናት፣ ዘመድ ወይም ወዳጅ ለመጠየቅ፣ ለስብሰባ፣ ዓለም አቀፍ ጉባዔዎችን ለመካፈል፣ ለጥናትና ምርምር፣ ለሃይማኖታዊ ጉዳዮች፣ ለስፖርት ዝግጅቶች ወይም ለማንኛውም ሌላ ጉዳይ ወደ ሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በመጓዝ በደረሰበት ቦታ ከ24 ሰዓት ላላነሰ እና ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ የሚቆይ ማንኛውም ሰው ነው፡፡

3) "እለታዊ ጎብኚ" ማለት ከሚኖርበት አካባቢ ለጉብኝት፣ ለመዝናናት፣ ዘመድ ወይም ወዳጅ ለመጠየቅ፣ ለስብሰባ፣ ዓለም አቀፍ ጉባዔዎችን ለመካፈል፣ ለጥናትና ምርምር፣ ለሃይማኖታዊ ጉዳዮች፣ ለስፖርት ዝግጅቶች ወይም ለማንኛውም ሌላ ጉዳይ ወደ ሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በመጓዝ በደረሰበት ቦታ ከ24 ሰዓት ላነሰ ጊዜ የሚቆይ ማንኛውም ሰው ነው፡፡

4) "የክፍያ ተመን" ማለት በመዳረሻዎች ለጎብኚዎችና ለሌሎች አገልግሎት ፈላጊዎች ለመግቢያ፣ ለኪራይ፣ ለፎቶግራፍ፣ ለቪዲዮ፣ ለፊልም፣ ለጥናትና ምርምር፣ ለዱር እንስሳት ቱሪዝም እና ለመሳሰሉት የሚወሰን የአገልግሎት ዋጋ ነው፡፡

5) "መዳረሻ" ማለት ጎብኚዎች ጊዜአቸውን የሚያሳልፉበት ተፈጥሮዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ የመስህብ ሀብት የሚገኝበት ቦታ ነው፡፡

6) "የመዳረሻ አስተዳዳሪ" ማለት መዳረሻዎችን እንዲያስተዳድር በህግ ኃላፊነት የተሰጠው መንግስታዊ አካል ነው፡፡

7) "ሚኒስቴር" ማለት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ነው፡፡

8) "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 47 (1) የተመለከተውን ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችንም ይጨምራል፡፡

9) "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

10) ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው አነጋገር የሴትንም ጾታ ይጨምራል፡፡

3. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ የጎብኚዎች የክፍያ ተመን አወሳሰን፣ ምክንያታዊ መስፈርቶችን በመከተል፣ በተገቢው ስረአት እንዲመራ የሚያስችል ወጥ፣ ግልፅ፣ ፍትሐዊ የሆነ አሰራር መዘርጋት ነው፡፡

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
Records Section

4. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

1) ይህ መመሪያ በፌዴራል መንግስት ሥር በሚተዳደሩ መዳረሻ ቦታዎች የጎብኚዎች ክፍያ ስርዓት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች የመዳረሻ ቦታዎችን የሚያስተዳድሩ አካላት በዚህ መመሪያ የተቀመጡትን መርሆችና መስፈርቶች ተከትለው እንደአግባብነቱ የራሳቸውን የክፍያ ስርዓት ወይም ተመን ሊወስኑ ይችላሉ፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለክፍያ ተመን አወሳሰን ሥርዓት

5. <u>የክፍያ ተመን መርሆዎች</u>

1. ተወዳዳሪነት
2. ተደራሽነት
3. አሳታፊነት
4. ዘለቄታዊ ተጠቃሚነት
5. ተመጣጣኝ ክፍያ ለተመጣኝነት አገልግሎት /ምክናታዊ/
6. ወቅታዊነት
7. ግልፀኝነት

6. <u>የክፍያ ተመን አወሳሰን መስፈርቶች</u>

ማንኛውም የመዳረሻ አስተዳዳሪ የክፍያ ተመን ሲወስን ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች መከተል ይኖርበታል፡-

1) የመዳረሻውን አጠቃላይ የሀብት ደረጃ፣ የአገልግሎቶች ስብጥር እና ጥራትን የመለየት፣

2) ከመዳረሻው ጋር ተወዳዳሪነት ያላቸው የሀገር ውስጥና የውጭ መዳረሻዎች የሚያስከፍሉትን ክፍያዎች ልምድ የመቀመር፤

3) የቱሪስቶችን የመክፈል አቅም፣ የመክፈል ፍላጎት (Willingness to pay) እና የመደረሻውን ተፈላጊነት መለየት፤

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
Records Section
የሰነድና ግሀደር ክፍል

4) የመዳረሻውን አስተዳደራዊ፤ ለጥበቃና ልማት የሚያስፈልጉ ወጪዎችን ሁሉ በአግባቡ መለየት፤

5) የመዳረሻዉን አካባቢ ህብረተሰብ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ከግምት ማስገባት፤

## 7. የክፍያ ትመና ሥርዓት

ማንኛውም የመዳረሻ አስተዳዳሪ የክፍያ ተመን ለመወሰን የሚከተሉትን ስርዓቶች መከተል አለበት፡፡

1. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6 በተመላከቱት መስፈርቶች ላይ ዝርዝር ጥናት የማካሄድ፤
2. በመዳረሻው የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ ረቂቅ የክፍያ ተመን ዝርዝር ማዘጋጀት፤
3. ረቂቅ የክፍያ ተመኑን ከተዘጋጀው ዝርዝር ጥናት ጋር በሚመለከተው መንግስታዊ አካል ማፀደቅ፤
4. የፀደቀውን የክፍያ ተመን የተለያዩ የግንኙነት ዘዴዎች በመጠቀም ለተጠቃሚዎች ማሳወቅ፡፡

## 8. የክፍያ ተመን ስለመከለስ

1) የመዳረሻ አስተዳዳሪ ወቅታዊ ሁኔታን በማገናዘብ በሁለት ዓመት ልዩነት የክፍያ ተመን ማስተካከያ ሊያደርግ ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የመዳረሻ አስተዳደር አስገዳጅ ሁኔታ ሲያጋጥመው በዓመት አንድ ጊዜ የክፍያ ተመን ክለሳ ሊያደርግ ይችላል፡፡

3) የክፍያ ተመን ክለሳ ሲደረግ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6 እና 7 የተመለከቱትን መስፈርትና ስረዓት መከተል ይኖርበታል፡፡

## 9. የክፍያ ተመን አፈፃፀም

1) ለጉብኝት አገልግሎት የሚፈፀም ክፍያ እንደመዳረሻው የአከፋፈል ሁኔታ በአካል ወይም በባንክ ወይም በኤሌክትሮኒክስ ሊፈጸም ይችላል፡፡

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
Records Section
የሪከርድና ማህደር ክፍል

2) የጎብኚዎች የክፍያ ተመን ለሀገር ውስጥ ዜጎችና ነዋሪዎች በብር ሲሆን ለውጭ ሀገር ዜጎች በአሜሪካን ዶላር በባንክ የሚፈፀም ይሆናል፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚቀበላቸው ሌሎች የውጭ ሀገር ገንዘቦች ክፍያ የሚፈፀም ከሆነ በዕለቱ ከዶላር ጋር ከሚኖረው ምንዛሬ ጋር ተጣጥሞ ይከፈላል፡፡

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የውጭ ሀገር ዜጋ በብር ክፍያ መፈፀም የሚፈልግ ከሆነ የውጭ ሀገር ገንዘቡን የዘረዘረበትን ገላጭ የሆነ (ኦርጂናል) ዋና ቅጂ ማስረጃ ለመዳረሻው አስተዳዳሪ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

4) መዳረሻው ክፍያ ለሰበሰበባቸው አገልግሎቶች ህጋዊ ደረሰኝ መስጠት ይኖርበታል፡፡

10.<u>የቱር ኦፕሬተር ኃላፊነት</u>

ማንኛውም ቱር ኦፕሬተር እንደየጎብኚዎቹ ዓይነት በዚህ መመሪያ አንቀጽ ዘጠኝ ንዑስ ቁጥር ሁለትና ሶስት በተጠቀሰው መሰረት ክፍያ ይፈፅማል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለተግባርና ኃላፊነት

11.<u>መቋቋም</u>

የጎብኚዎች የክፍያ ተመን ስርዓትን በበላይነት የሚከታተልና አፈፃፀሙን የሚገመግም የባለድርሻ አካላት የግንኙነት መድረክ ከዚህ በኃላ “መድረክ” የሚባል በዚህ መመሪያ ተቋቁሟል፡፡

12.<u>የመድረኩ አባላት</u>

1) መድረኩ የሚከቱሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ. የሚኒስቴሩ የቱሪዝም ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ................. ሰብሳቢ

ለ. የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን .............................. አባል

ሐ. የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን .................. አባል

መ. ብሔራዊ ቤት-መዘክር ................................................. አባል

ሠ. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ............................................ አባል

ረ. የቤተ መንግስት አስተዳደር........................................ አባል

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
Records Section
የሪከርድና ማህደር ክፍል

ሰ. የአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን..................አባል

ሸ. ቱሪዝም ኢትዮጵያ.........................................አባልና ጽሐፊ

ቀ. የኢትዮጵያ ቱር ኦፕሬተርስ ማህበር .........................አባል

በ. የኢትዮጵያ አስጎብኚዎች ማህበር ..............................አባል

ተ. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ............ አባል

ቸ. የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ..........አባል

2. መድረኩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሌሎች አግባብነት ያላቸውን አካላትን በአባልነት ሊያካትት ይችላል፡፡

## 13. የመድረኩ ተግባርና ኃላፊነት

1) የጎብኚዎች የክፍያ ስርዓት አተገባበር በበላይነት ይከታተል፣ ይገመግማል፤
2) በመዳረሻ አስተዳዳሪዎች የሚቀርቡ ጥናቶችና ረቂቅ የክፍያ ተመኖችን ተገቢነት ይገመግማል፣ አቅጣጫ ይሰጣል፣
3) የጎብኚዎች ክፍያ ስርዓት በሚሻሻልባቸው አግባቦች ላይ ሀሳቦችን ያቀርባል፤ አቅጣጫ ይሰጣል፤
4) ከክፍያ ስርዓት ጋር ተያይዞ ለሚያጋጥሙ የአሰራር ማነቆዎች ተገቢውን የመፍትሔ አቅጣጫ ያመላክታል፣
5) እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች በክፍያ ስርዓት ዙሪያ ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ሲነሱ ተወያይቶ አቅጣጫ ይሰጣል፡፡

## 14. ስለመድረኩ ስብሰባ

1) መድረኩ መደበኛ ስብሰባውን በስድስት ወር አንድ ጊዜ ያደርጋል፣ ሆኖም እንዳስፈላጊነቱ በሰብሳቢው ጥሪ በማንኛውም ጊዜ ስብሰባውን ሊያደርግ ይችላል፡፡
2) በስብሰባው ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡
3) የመድረኩ ውሳኔ በአባላቱ ሁለት ሦስተኛ ድምጽ ይወሰናል፡፡ የመድረኩ ድምፅ እኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።
4) መድረኩ የራሱን የስብሰባ ስነ ስርዓት ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 15. የሚኒስቴሩ ተግባርና ኃላፊነት

ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
Records Section
የሪከርድና ማህደር ክፍል

1) የክፍያ ስርዓትን የሚመለከቱ ተሞክሮዎችን መቀመር፣ መረጃዎችን በማደራጀት ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ የማድረግ፣

2) በዚህ መመሪያ የተደነገጉ መስፈርቶችና የአሠራር ስርዓቶች በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲፈጸሙ ለክልሎችና ለሌሎች የመዳረሻ አስተዳደር አካላት ተገቢውን ድጋፍ የመስጠት፣

3) በመድረኩ የሚሰጡ አቅጣጫዎችን ተግባራዊነት የመከታተላል፣

4) በቴክኖሎጂ የተደገፈ የክፍያ ስርዓት ተግባራዊ እንዲሆን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅርበት የመስራት፣

5) ከክፍያ ነፃ ስለሚስተናገዱ ጉዳዮች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ዝርዝር መስፈርት በማውጣት የማስተግበር፤

6) በመዳረሻ አካባቢ ቀልጣፋና ዘመናዊ የባንክ ስርዓት የሚዘረጋበትን መንገድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የማመቻቸት፤

7) የዚህን መመርያ አፈጻጸም የመደገፍ፣ የመከታተል፣ የማስተባበርና የመቆጣጠር፤

16. <u>የመዳረሻ አስተዳደር ተግባርና ኃላፊነት</u>

የመዳረሻ አስተዳዳሪ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1) በዚህ መመሪያ መሰረት የክፍያ ተመን የማዘጋጀት፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ የማድረግ፣

2) የጎብኚዎች ክፍያ ህጋዊ ስርዓትን ተከትለው መፈፀማቸን መከታተል፣

3) በክፍያ ትመናና ትግበራ ዙሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የመስራት፣

4) የመዳረሻዎችን ክፍያ በሚመለከት መረጃዎች የመያዝና፤ እንደአስፈላጊነቱ ለሚኒስቴሩና ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ የማድረግ፣

5) በመዳረሻዎች አካባቢ ከክፍያ ጋር በተያያዘ ከጎብኚዎች ለሚነሱ ቅሬታዎች ተገቢውን ምላሽ የመስጠት፣

6) የክፍያ ስርዓትን በተመለከተ በጉብኝት ሂደት ለሚሳተፉ አካላት ግንዛቤ የመፍጠር፡፡

7) ክፍያውን በጎብኚዎች ዓይነት በመለየት በብርና በዶላር ማስቀመጥ፤

የባህል ... ቱሪዝም ሚኒስቴር
Records Section
የሪከርድና ማህደር ክፍል

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

17. **ክልከላ**

1) የዚህን መመሪያ መስፈርትና ስርዓትን ያልተከለ ማንኛዉንም የክፍያ ተመን ማስፈፀም የተከለከለ ነው።

2) ጎብኚዎች ክፍያ ለፈፀሙበት አገልግሎት ተጨማሪ ክፍያ ማስከፈል የተከለከለ ነው።

18. **ተጠያቂነት**

ማንኛውም የዚህን መመሪያ አፈጻጸም የተላለፈ ሰው አግባብነት ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል

19 **የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ለዚህ መመርያ ተግባራዊነት የመተባበር ግዴታ አለበት፣

20. **መመሪያውን ስለማሻሻል**

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል።

21. **መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከፀደቀበት ከመጋቢት 08 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

ሂሩት ካሳው ወንድም (ዶ/ር)
የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
ሚኒስትር

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
Records Section
የሪከርድና ማህደር ክፍል